**FEDERATION OF AMHARAS IN NORTH AMERICA (FANA)**
fanalightofamhara@gmail.com

**04/17/2024** **Ref # FANA_2024_00130**

# ከአማራ ማኅበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ(ፋና) የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

እንደሚታወቀው ትህነግና ግባራበሮቹ በይፋ የአማራን ህዝብ እንደ ጠላት ፈርጀው መጨፍጨፍ ማፈናቀልና አፅመ ርስቱን በመቀራመት በኢትዮጵያ ውሰጥ ለ27 ዓመታት ያለ ምንም ከልካይ እንዳሻቸው ሲፈጽፈሙ ቆይተው በአብይ አህመድ በሚመራው የኦሮሞ ብልፅግና ተተክተዋል። ተረኛ ነኝ ባዩ እና የኦሮሞን የበላይነት ለማስፈን የሚጥረው በአብይ አህመድ የሚመራው አገዛዝ ስልጣኑን ከተረከበ ከ2010 ዓ/ም ጀምሮ በታሪክ አቻ የማይገኝለት እጅግ አረመኒያዊ ጭፍጨፋ እና ማፈናቀል በአማራ ሕዝብ ላይ እያካሄደ ይገኛል። ይህ የአብይ አገዛዝ ላለፉት ድፍን ስድስት ዓመታት በአማራ ሕዝብ ላይ ብቻ ለይቶ እየፈጸመ ያለው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እና ገጠር ከከተማ ሳይለይ የአማራን ሕዝብ ከመኖሪያው የማፈናቀል እርምጃ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሆነ ለአማራ ሕዝብ የሚቆረቆሩ የአማራ ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ የአለማቀፍ ተቋማት ጭምር ስጋታቸውን በተለያየ አጋጣሚዎች አሰምተዋል። በተለይ ደግሞ የአብይ አገዛዝ ባለፈው አንድ ዓመት በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የኦሮሞ ልዩ ኃይልን ከባባድ መሳሪያዎች አስታጥቆ በማዝመት እና ድሮኖችን እና ተዋጊ ጀቶችን በመጠቀም በተለያዩ ቦታዎች ያልታጠቁ ንጹሐን አማራዎችን በጅምላ ጨፍጭፏል።

ይህንን ከአገዛዝ ወደ አገዛዝ ለዘመናት የተሸጋገረ አማራን የማጥፋት አረመኔያዊ ዘመቻ ቀልብሶ እንደ ሕዝብ የመኖርና ሰብአዊ መብቱን ለማስከበር በውጭም በውሰጥም ያለው አማራ ተደራጅቶ እየታገለ ይገኛል። በሀገር ውስጥ ያለው የአማራ ፋኖ በአማራ ህዝብ ላይ የተከፈተውን የአብይ አህመድ የዘር ማጥፋት፣ ዘር ማጽዳት እና አገር ማጥፋት ዘመቻ በከፍተኛ መስዋእትነት በብቃት እየመከተ በሚገኝበት ሰዓት የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ድርጅት (ትህነግ) የራያ አላማጣ አካባቢን ከሚዚያ 7 ቀን 2016 ዓ/ም ጀምሮ በኃይል መውረሩ እና የተለመደ አረመኔያዊ ተግባሩን በአማራ ህዝብ ላይ መፈጸሙን ከአካባቢው የወጡ መረጃዎች አሳውቀዋል። ትህነግ ወረራውን ይፈጸም ዘንድ ሙሉ ፈቃዱን የሰጠው እና ሁኔታዎችን ያመቻቸው የአብይ አገዛዝ በሥፍራው ባሰማራው በስልጣን ጠባቂ ወታደሮቹ የአካባቢውን አስተዳዳሪዎች እንዳስረሸናቸውም ታውቋል።

አማራ በቅንብር የተከፈተበትን ጦርነት ያለ ምንም ጥርጥር በአሸናፊነት እንደሚወጣው በቅድሚያ ለሁሉም ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ትህነግ ጠላቴ ብሎ ለሦስት አስርት ዓመታት ሲጨፈጭፈው የኖረውን የአማራ ህዝብ በዚህ ጊዜ ለመውረር ፣ ለመዝረፍና ለመግደል አሁንም የትግራይን ወጣት ማዝመቱ በአማራ እና በትግራይ ህዝብ መካከል ዘላቂ ጠላትነት እና ወደ ማያባራ መጠፋፋት ውስጥ ለማስገባት ለሚጥረው የአብይ አገዛዝ እንጂ ለትግራይ ሕዝብ አይጠቅምም።

የአማራ ማኅበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ(ፋና) የአማራና ትግራይ ህዝቦች ለሽህ ዘመናት በአንድነት የኖሩ፣ በልማድ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲሁም በእምነት ሊነጣጠሉ እንደማይችሉ ያምናል፡፡ ታሪክ ይጋራሉ ብቻ ሳይሆን አገር በጋራ ፈጥረዋል፤ በመስዋእትነታቸውም ይህችኑ አገር ለእኛ ትውልድ በነጻነት ተጠብቃ እንድትኖር አድርገዋል፡፡ ይሁንና ባለፉት 40 እና 50 አመታት ትህነግ ለጊዚያዊ ፖለቲካዊ ትርፉ ሲል ለዘመናት በጥብቅ ቁርኝት በኖረው ህዝብ መካከል ጠብን በመዝራት አሁን ሁለቱም ህዝቦች ለገቡበት ችግር ሁሉ ሰበብ ሆኗል፡፡ ይሄው ኃይል በአማራ ህዝብ ላይ ተነግሮ የማያልቅ በደል መፈጸሙም የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡ በመጨረሻም የትህነግ የከፉ ሥራ ዳፋው ለትግራይ ህዝብም ተርፏል፡፡

የአማራ ህዝብ በኦሮሙማው ፋሽስት ዘር ጨፍጫፊ አገዛዝ ላይ የተባበረ ተቃውሞ በሚያነሳበት የቅድመ ምርጫ ጊዜ ይሄው የትህነግ ኃይል ከስህተቱ ባለመማር ከአማራ ህዝብ ጋር ውዝግብ ውስጥ በመግባት የአብይን እድሜ በተዘዋዋሪ አራዝሟል፡፡ በኋላም “ከአማራ ጋር ሂሳብ አወራርዳለሁ” በሚል ጦርነት ከፍቶ ህልቆ መሳፍርት የሌለው ጉዳት አድርሷል፡፡ በሚያሳዝን መልኩ አሁንም የአብይን ፋሽስታዊ አገዛዝ ለማራዘም በሚመስል መልኩ በሴራው ወጥመድ ሰተት ብሎ ገብቶ በራያ ወረራ ውን ጀምሮ በወልቃይትም ለጥፋትና ለእልቂት እየተዘጋጀ ይገኛል።

ፋና ለትግራይ ህዝብ፣ ለትህነግ መሪዎች እና ለትግራይ ልሂቃን የሚከተለውን ሀሳብ በቀናነት ሊገልጽ ይወዳል፡፡ ቅድመ ትህነግ አማራና ትግሬ ምንም እንኳ ግልጽ የሆነ ታሪካዊ፣ ብሄረ ማንነትና ድንበር ቢኖራቸውም ሁለቱም ህዝብ ድንበር ለይቶ ለመኖር የሞከረበትም ሆነ የተቆራቆሰበት ዘመን ታይቶ አይታወቅም፡፡ የአማራ የሆነውን ለትግሬ፤ የትግሬ የሆነውን ለአማራ እየተጋሩ ሺህ ዘመናትን በክፉም በደጉም በአንድነት አሳልፈዋል፡፡

ይህንን መሰረታዊ ሀቅ በመንተራስ አሁንም በአማራና ትግራይ ህዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት ወደ ቅድመ ትህነግ ሁኔታ መመለስ እንዳለበት ያምናል፡፡ ይልቅም አንዱ የአንዱን ድንበር ለመጣስ ከመመኘት እና ግርግር ከመፍጠር ይልቅ ነባራዊ ድንበሮችን አክብሮ የህዝቡን አንድነት በማጠናከር በኢትዮጵያ ውስጥ ተዘዋውሮ የሚሰራበትን እና የሚኖርበትን ሁኔታ መፍጠር፤ ሁለቱ ህዝብ ደሙን አፍሶ ያበጃትን አገር ከኦሮሙማ ፋሽዝም እንዲታደግ የኦሮሙማውን ፋሽስት ቡድን በመጣል እና አዲስና ለሁሉም የምትበጅ አገር የመገንባት ሂደቱን በጋራ እንዲወጣ ሲል ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ከዚህ በመለስ ያለው ግን ለፋሽስቱ ቡድን ጥንካሬ በመስጠት፣ የአማራንም የትግራይንም ህዝብ ከአገራቸው ኢትዮጵያ ጨርሶ መንቀልን የሚያስከትል አደገኛ እና ሩቅ አሳቢነት የጎደለው አካሄድ እንደሆነ ፋና ያምናል፡፡ ከዚህም ጋር አያይዞ ፋና ለመላው የአማራ ህዝብ፣ የአማራ ልሂቃን ፤የትግራይ ህዝብ፣ የትግራይ ልሂቃን አሁን ያለውን ሁኔታ በበቂ ሁኔታ አጢነው አብረው ለመስራት መነጋገር የሚጀምሩበት ጊዜ እንደሆነ በመገንዘብ፤ እርስ በርስ የመጠፋፋቱን ውጥን በጥበብ እንዲያከሽፉት ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ይሄ ሳይሆን ቀርቶ ግን ትህነግ በተጠመደለት የፋሽቱ ኦሮሙማ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብሎ የሚገባ ከሆነ ምናልባትም በአማራና ትግራይ ህዝብ መካከል ዘላቂ የሆነ፤ ለእርቅ የሚያስቸግር ቁርሾ እንዳይተክል ያሰጋል፡፡  ስለሆነም የትግራይ ህዝብ እና የትግራይ ልሂቃን ለመነጋገርም ሆነ ለመወቃቀስ የጋራ አገር ማስቀጠሉ እንደሚቀድም በመረዳት የፋሽስቱን ኦሮሙማ አገዛዝ ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ላይ ቀጥተኛና አፋጣኝ ተሳትፎ እንዲያደርጉ  ፋና ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ከአማራ ፋኖ ውጭ ሌላ የአማራን ጉዳይ ይዞ ሊነጋገር የሚችል ሌላ ህጋዊ አካል አለመኖሩን፣ ይልቅም የአማራ ብልጽግና የተባለው የፋሽስቱ ኦሮሙማ ነጭ ለባሽ እና ተላላኪ መሆኑን ግንዛቤ እንዲወሰድ ሲል ፋና አጽንኦት ሰጥቶ ያሳውቃል፡፡

ይህ አረመኔ አገዛዝ እስካልተወገደ ድረስ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምትና የራያ የአማራ ህዝብ ሰላምና ዕረፍት ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይሄ አገዛዝ በህይወት እያለ የሚመለስ ጥያቄም አይኖርም፡፡ ይሄንንም ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም አካባቢ ያለ አማራ ትግሉን አጧጡፎ እንዲቀጥልና አረመኔውን የኦሮሙማ ፋሽስት ቡድን በማስወገድ የሰቆቃ ጊዜውን እንዲያሳጥር ጥሪያችንን  እናቀርባለን።

ድል ለአማራ ሕዝብ!

የአማራ ማኅበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ(ፋና)